BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## Do you play football?

## እግር ኳስ ትጫዎታለህ/ቻለሽ?

*This is not a word-for-word transcript*

**ምህረተስላሴ**

ጤና ይስጥልን። ለማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ የሚያስፈልጉ የቋንቋ መሰረታዊያን ወደምናቀርብበት Essential English Conversation እንኳን በደህና መጡ። ምህረተስላሴ እባላለሁ። በዚህ ክፍል ሰዎች አንድ የጨዋታ አይነትን ስለመጫዎታቸውን እንዴት መጠየቅ እንደሚቻል ይማራሉ።
ሁለት ሰዎች የተለያዩ ስፖርቶችን ይጫዎቱ እንደሆነ እርስ በርስ ሲጠያየቁ ያዳምጡ።

***Pam***
*Do you play football?*

***Ben***
*Yes, I do. How about you?*

***Pam***
*No, I don't, but I go running.*

**ምህረተስላሴ**

ንግግሩ ካስቸገረዎ ብዙም አይጨነቁ፤ ንግግራቸውን ከፋፍለን እንዲለማመዱ እናግዝዎታለን።
በመጀመሪያ "ኳስ ትጫወታለህ ወይ" ስትል ፓም ቤንን ጠየቀችው። 'play' የተባለውን ቃል ከማንኛውም የስፖርት አይነት ጋር እንጠቀማለን። ስለዚህ ቅርጫት ኳስ መጫዎት 'play basketball' እና ቴኒስ መጫዎት 'play tennis' እንላለን። ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ።

*Do you play football?*

**ምህረተስላሴ**

ከዚያም ቤን "አዎ እጫወታለሁ" 'Yes, I do.' አለ። ለጥቆም ተከታይ ጥያቄ ሰነዘረ "አንችስ?" 'How about you? ይህንን አገላለጽ መጀመሪያ ጥያቄውን ላቀረበው ሰው ተመሳሳይ ጥያቄ ለመጠየቅ እንደተጠቀምንበት ያስታውሱ። ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ።

*Yes, I do.*

*How about you?*

**ምህረተስላሴ**

ፓም ለቤን አዎ ወይም አይ የሚል መልስ ሰጠችው። "አይ፤ አልጫወትም" 'No, I don't' ብላ መለሰች። ከዚያም ነገር ግን 'but' የተባለውን አያያዥ ቃል ተጠቀመችና ሌላ የምታከናውነውን ነገር አስተዋወቀች፤ እሮጣለሁ 'I go running' አለች። 'go' የሚባለውን ቃል በ'-ing' የሚጠናቀቁ እንቅስቃሴዎችን ለመግለፅ እንጠቀምበታለን። ስለዚህ 'go swimming' መዋኘት፣ 'go hiking' ተራራ መውጣት እንላለን። ያዳምጡ እና ደግመው ይበሉ።


© British Broadcasting Corporation 2018

*No, I don’t*

*But I go running.*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን የተለያዩ ሰዎች ስለሚያዘወትሯቸው ስፖርቶች ሲወያዩ በማዳመጥ እርስዎ ያሉት ትክክል እንደሆነ ይፈትሹ።

*Do you play tennis?*

*No, I don’t, how about you?*

*Yes, I play tennis.*

*Do you play basketball?*

*Yes, I do. How about you?*

*No, I don’t, but I go swimming.*

**ምህረተስላሴ**
እሺ፤ ይህንኑ ደግመን እንሞክረው። የእንግሊዝኛውን አረፍተ ነገር ያዳምጡና ደግመው ይበሉ። እያንዳንዳቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ያዳምጧቸዋል።

*Do you play football?*
*Do you play football?*

*Yes, I do. How about you?*
*Yes, I do. How about you?*

*No, I don’t, but I go running.*
*No, I don’t, but I go running.*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንዳስታወሱ እንይ። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይበሉ።

*እግር ኳስ ትጫወታለህ?*
*Do you play football?*

*አዎ፤ አንቺስ?*
*Yes, I do. How about you?*

*አይ፤ አልጫዎትም፤ ግን እሮጣለሁ።*
*No, I don’t, but I go running.*


© British Broadcasting Corporation 2018

**ምህረተስላሴ**
በጣም ግሩም፤ አሁን ሰዎች ስለሚያዘወትሩት ስፖርት መጠየቅ ተምረዋል። ለፓም ምላሽ በመስጠት ልምምድ ያድርጉ። 'How about you?' በማለት ተከታይ ጥያቄ ማቅረብና እና ወይይቱን 'That sounds great!' ብሎ መደምደም አይርሱ።

*Do you play football?*

*No, I don't, but I go running.*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን አጠቃላይ ውይይቱን አንዴ ያዳምጡና መልስዎን ያመሳክሩ።

***Pam***
*Do you play football?*

***Ben***
*Yes, I do. How about you?*

***Pam***
*No, I don't, but I go running.*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን ሰዎች የትኞቹን የስፖርት ዓይነቶች እንደሚጫወቱ በእንግሊዝኛ መጠየቅ ችለዋል። ጓደኛ ይፈልጉና ምን ዓይነት ስፖርት እንደሚያዘወትሩ በእንግሊዘኛ በመጠየቅ ይለማመዱ። 'How about you?' በማለት ተከታይ ጥያቄ ማቅረብ አይዘንጉ። ለተጨማሪ የኢሰንሻል ኢንግሊሽ መሰናዶ በሚቀጥለው ክፍል ይጠብቁን። Bye!


© British Broadcasting Corporation 2018